ለአቶ. ገብረ ሥላሴ ገብረ መድሕን!
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ።

ያነሷቸውን መልክትችዎን አነበብኳቸው። ቢቢሲዎችም ሆኑ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የሰጡትን መልሶች አሳውቀውናል። ጥሩ ሃሳብ ነው። አዎ አቶ ኃይሉ ያነሱን በአንድ ፊት ብቻ ሳይሆን በሌላም አቅጣጫ ሊመለከቱላቸው ይገባል። በደርጉ ጊዜ ከዚያ ጨካኝ መንግጽት ግር አብረው መስራታቸው ራሱ ስህተት ነብረ በበኩሌ ሳስበው የኢሥፓ አባል ሆነው አሁን ተመልሰው የቅንጅት መሪ ሆነዋል።

ጥያቀዬ ግን ታዲያ የደርግ ልጆች ናቸው ማለት ይሆን በዲያስፖራው ውስጥ አሰማርተው የኢትዮጵያን የተለያዩ ብሔረሰቦች ሲያሰድቡ የቆዩት አሁንም እንደቀጠሉ የሚገኙት የሳቸው ተከታዮች? እነኛ ነገሮች ያስገርማሉ ሲሆን ሲሆን በሰላም መታገል ማለት ልክ ያለምንም አይነት አጪቃጫቂ ሁኔታ ፍላጎትን በፊት ለፊት መግለጽ እንደሆነ ነው የማውቀው። በቅንጅቱስ የውጭው አሰራር ሁኔታዎችና የራዲዎኖቻቸው አስተላለፍ ሥራዓቶችና ብሎም ፓልቶኮቻቸው ምን ይመስላሉ? እነኛ ሁሉ የአስተሳሰብ ልዩነትና ብሎም የጽንፈኞች ርምጃ የመሰሉ በመሳደብና በማሳበቆች በመሳሰሉ ክብር የማይሰጡ የአነጋገር ዘይቤዎች ሁሉ እነኛም ልክ እንደጥፋት ተቆጥረው ሊታረሙ ሊያርሟቸውም ይገባል ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል?

በሌላ አነጋገር የሌሎቹ ኃሳብ ተንጠልጥለው የኛ የኔ አስተሳሰብ ግቡን ይምታልኝ እንጅ በሚል የሚሄዱ ከሆነ ለወደፊትም ቢሆን ችግሮች አሉ ማለት ነው። ግልጽና ብሎም ከጥሩ የአስተሳሰቦችና ጨዋነቶች ጋራ እሳቸውም ሆኑ ተከታይ ሠራዊቶቻቸው በውጭ የሚገኙት የኢሠፓ ልጆችም ጸባያቸውን እንዲያስተካክሉ መምከር ይኖርባቸዋል። በጣም በሚያሳዝንም ሁኔታ የተከፋፈለ ሥራዎች እየሰሩም ነው። አንድ ድርጅት ሆኖ በአንድ ድርጅት ስም 2 የተለያዩ አመለካከት ያላቸው ቅምጦችን አበጅተው ይንቀሳቀሳሉ የነሱ ሽኩቻዎች የኢትዮጵያን ጥያቄ ሊያነሳ አይችልም።

ይልቅስ የምንመክራቸው ቢኖር ስለ ኢትዮጵያ በብሄራዊ ደረጃ ሄደው ሊያስቡላት ይገባል? ያን ካላደረጉ እነርሱ በሚያደርጉት የወሬ ማመሰቃቀል አሰራር ሁኔታ በአገራችን በኢትዮጵያ ላይ አደገኛ ሁኔታ እንዳይፈጠር ማሰብ ይገባል።

ቅንጅቱ እንዳካሄደው አስመራም ገብቶ እንደነበረ ማሰብ ማስታወስ ይኖርባቸዋል። ከዚያም AFD የተባለን በመመሥረት እነ አቶ ሰለሞን ተካልኝ ሳይቀሩ ወደዚያ ዘምተው የሙዚቃ ድግሶቻቸውንም አከናውነው እንደነበረ አይዘነጋም። ያነው እንግዲህ እውነቱ የአሰራር ሁኔታውን የሚያጋልጠው። ለመሆኑ ቅንጅቶቹ ለነሱ ዓላማ ብቻ ነው የቆሙት ወይስ የኢትዮጵያንም ሕዝብ ሰላምና በአገሩ ተባብሮ በመኖር ከችግሮቿ ለማውጣት ነው?

በስልጣን ላይ ያለውንም መንግሥት የምርጫ ዘመኑን እስኪጨርስና ከዚያም ወይ የራሱ ፓርቲ ካልሆነም ከተቃዋሚዎቹ በአሸናፊነት የሚመረጠው በሚቋቋምበት ጊዜ ያገሪቱ ሁኔታ ምንም ነገር ሳይቀይር ሠላማዊ ሽግግርችና ብሎም የቀድሞው የገዥ ፓርቲ በምንም ዓይነት ሁኔታ ወደተጠያቂነት ወደስድቦችና ብሎም ማንቋሸሽ ሳይገባ

በገዛ አገራቸው ውስጥ በፈለጉበት የመኖር ዘዴዎች ተጠቅመው የጡረታ መብታቸው ተከብሮላቸው ላጠፉት ተወቅሰው ላለሙትም ተመስግነው እዚያ በአገራቸው የሚኖሩበትን ዘዴዎች ሳይቀሩ ሊታሰቡ ይገባቸዋል።

በአገራችን ከጽንፈኞች ጋራ ለመጀመሪያ ጊዜ ያዋጣኛል ብለው በውጭ የሚኖሩ የዲያስፖራው ቅንጅት ደጋፊዎችና አባሎች ያደረጉት ለነሱም የኢትዮጵያ ሕዝብን ይቅርታ ተለይተው መጠየቅ ይኖርባቸዋል?

ባጠቃላይ ለወደፊቱ በዚህ ሁኔታ የምንነጋገርበትን \አይጋፎሩም| ራሱን የቻለ የማወያያ ገጽ በመስጠት የህዝብን ሃሳብ በማመላለስ ለህዝቧ ታስረዳለች ብዬ እምነቴን እገልጻለሁ።

አበራ ቱፋ
ከአዲስ አበባ/ አባኰራን ሰፈር።